ሐምሌ ፳፻፯ ዓ.ም.

# <u>አራዊታዊው ኢሀደግ እና የየመን መንግሥት በአቶ አንዳርጋቸው ላይ በፈጸሙት አራዊታዊ ትግባር የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ቀሳውስት</u>

1ኛ ዶክተር ቀሲስ አማረ ካሣየ

2ኛ ቀሲስ አስተርአየ ጽጌ

3ኛ አባ ኃ/ሚካኤል የሰጡት መግለጫ፡-

በአገራችን ላይ ከፉ ዘመን የወለደው አራዊታዊው መንግሥትና የየመን መንግሥት በአቶ አንዳርጋቸው ላይ የፈጸሙት አራዊታዊ ተግባር በፈጣሪና በፍጡሩ ዘንድ ተቀባይነት የሌለው፤ የሰው ጥንተ ጠላት የሆነው የሰይጣን ተግባር ስለሆነ፤ በቅድስት ቤተ ክርስቲያችን የሚወገዝ ነው። ሕዝባችንም የዜግነት ከለላ ከሰጣቸው ከእንግሊዝ መንግሥት ጋራ በመተባበር አቶ አንዳርጋቸውንና በተመሳሳይ አራዊታዊ አደና የተያዙትን ሁሉ ኢትዮጵያውያን ለማስለቀቅ የጀመረውን ጥረት አስፈላጊ በሆነው ሁሉ መንገድ እንዲቀጥል እግዚአብሔር የሚቀበለውና የቅድስት ቤተ ክርስቲያንም ተቀዳሚ ተግባር ነው።

ሰውን ሰው አድኖ ሲበላው ዝም ማለትና ቆሞ መመልከት “ለእርሱ ስለሆኑት ይልቁንም ስለ ቤተ ሰቦቹ የማያስብ ማንም ቢሆን ሃይማኖትን የካደ ከመያምን ሰው ይልቅ የሚከፋ ነው “ (1ጢሞ 5፡8) ብሎ ቅዱስ ጳውሎስ ከተናገረው ጋራ የሚጋጭ፤ ከእምነታችን፤ ከታሪካችን፤ ከባህላችንም ውጭ፤ ከህገ አራዊትም እጅግ ርቆ የሄደ፤ በሰባዊ ቋንቋ ሊገለጥ የማይችል ርኩስና አስከፊ ተግባር ነው።

ከዚህ ቀደም ከሱዳን፤ ከጅቡቲና ከኬንያ ዛሬ ደግሞ ከየመን በዚህ አራዊታዊ መንግሥት እየታነቀ በመበላት ላይ ሰውነት እያየን፤ አራዊታዊው መንግስትም በጎረሰው ሥጋ ታንቆ የሚያሰማውን መጎጉጎ ር እየሰማን ዝም ማለት ቅዱስ ጳውሎስ እንዳለው ቤተ ሰብነትን መካድ፤ በፈጣሪ አለማመን ነው። <u>ጸሎታችንና ጥረታችን በአውሬ የተጎረሰውን የወገን ሥጋ ለማዳን ብቻ ሳይሆን፤ ምንም እንኳ አውሬም ቢሆን የወገንን ሥጋ ሲበላ ታንቆ ብናገኘው፤ ከመግደል ይልቅ መንገድ ከተገኘ አውሬውንም ታንቆ እንዳይሞት ለማዳን ክርስትናችን ያስገድደናል። ዝምታ ግን በሁለቱም ማለትም፡- እየተዋጠ በመሞት ላይ ባለው ሰውነትና፤ ሲውጥ ታነቆ በመሞት ላይ ባለው አውሬ ዘንድ ተቀባይነት የለውም።</u>

ይህን ሁሉ እያየንና እየሰማን ዝም ብንል፤ ከላይ የጠቀስነውን ቅዱስ ጳውሎስ ለሰባዊነት ሊደረግ የሚገባውን መልእክት አንድም እያሉ ያስተማሩን የመምህሮቻችን አጽም ይፋረዳናል። ይልቁንም ከልጅነታችን ጀምሮ በአውደ ምህረቱ ላይ አሁንም የምናነበው ከአውደ ምህረቱ ውጭ ወጥተን ከሚጮኸው ህዝብ ጋራ እንድንቀላቀል ያስገድደናል።

የወያኔ መንግሥት የፈጸመው ተግባር ከላይ እንዳልነው አውሬነትን፤ ፈሪነትን እንጅ ጀግንነትንና ተቀባይነት ያለው ፖለቲከኛነትን (የመሪነት ችሎታ) የሚገልጽ ባለመሆኑ በማነኛውም መንገድ የሚያስፎክርና ይበል የሚያሰኝ አይደለም። "አሚነስ መሰረት ይእቲ" እንደተባለው ፤ ሃይማኖት የሁሉም መለኪያችን መሠረት ናትና አራታዊውን መንግሥት በሃይማኖታችን ስንመዝነው፤ ቢያንስ በፈጸማቸው ሶሶት ነገሮች ከሰባዊነት ወደ ዱር አውሬነት መቀየሩን በራሱ ተግባር አረጋግጧል።

1ኛ፦ርዳታ ሰጭውን ዓለም አቀፍ ህዝብ አታሏል፤

2ኛ፦ ከተራበው ህዝብ አፍ ነጥቋል፤

3ኛ፦ ክፉ ተግባሩን የሚቃወሙትን ንጹህን ዜጎች ድንበር እየጣሰ ለማደን ለአውሬ ተግባሩ ተጥቅሞባትል።

ወያኔ አቶ አንዳርጋቸውን አድኖ ለመያዝ ያፈሰሰውን በሚሊዮን የሚቆጠረውን ገንዘብ ኢትዮጵያን ለማፍረስ እራሱን ከወለደበት ጫካ አፍሶ አላመጣውም። በተደጋጋሚ ሲነገር እ ደሰማነው፤ ዓለም ለልማት ወይም ለተራበው ህዝብ የለገሰው የእርዳታ ንዘብ እንደሆነና በግብር ስምም ከደሀው ህዝብ እያስገደደና እየዘረፈ የሰበሰበው እንደሆነ ተደጋግሞ ተነግሯል።

"ቤት ሲቃጠል ባለቤት ካልጮኸ ጎረቤት አይረዳም" እንደተባለው፦ ርዳታ ሰጭው ዓለም የሚሰጠውን ገንዘብ ወያኔ ለህዝብ ጥፋት መዋሉን ተረድቶ፤ መገሰጽ፤ ማውገዝና የእርዳታ መንገዱ መቀየር ያለበት መሆኑን ማሳወቅ ያለብን እኛው ነን። በጎረቤት አገሮች የሸሹትንና አሁን ደግሞ የእንግሊዝ ዜጋ የሆኑትን ከየመን አፍኖ በመያዙ፤ ራሱ በሚቆጣጠራት ኢትዮጵያ ውስጥ ያሉትን ወገኖቻችንን የቱን ያህል እንደበላቸው፤ እየበላቸው እንደሆነና፤ ወደፊትም በልቶ የሚጨርስ መሆኑን ሳንሰለችና ሳንደክም ለዓለም በግልጽ የማሳየት ሀላፊነቱ የኛ ነው።

አራዊታዊው ኢህደግ የራሱን ሰባዊ ባህርይ ወደ አውሬነት ቀይሮ በኢትዮጵያ ላይ ብቅ ማለቱ ሲያስገርመን፤ ኢትዮጵያ ከዚህ ቀደም በነበረው ታሪኳ፤ ለጎረቤት አገሮች ለነጻነት ለባህልና ለሃይማኖት ምሳሌ ሆና የኖረች ስትሆን፤ ሰውን አድኖ ለመብላት በዘር በጎሳ ለመከፋፈል ለርስ በርስ መጠላላትና ለመጠላለፍ ሰይጣናዊ ባህርይ ለጎረቤት አገሮች ምሳሌ አድርጎ አቅርቧታል። በኢትዮጵያ ምድር እንደ ጉድ ተወልዶ የአራዊት ጠባይ ይዞ ከዱር ብቅ ብሎ በኢትዮጵያ ላይ የመጣባት አውሬ እንጅ፤ ለሰባዊንት ክብርና ለጻነት ተሟጋች የነበረችው ኢትዮጵያዊ የወለደችው መንግሥት አለመሆኑን ማሳየት አለብን።

የዱር አራዊት ከነሱ ልዩነት ያላቸው አራዊት በተመሳሳይ ቅጽበት አካባቢያቸውን ጥሰው ሲመጡባቸው፤ ሁሉም ወደየመጡበት አካባቢ እንዲመለሱ በጩኸታቸው ያባርራሉ እንጅ፤ ከሌላ አካባቢ የመጣባቸውን አውሬ አንቀው ከለሌ አካባቢ ለመጣባቸው አውሬ አሳልፈው አይሰጡም። የየመን መንግስት ከወያኔ በተማረውን አራዊታዊ ተግባር፤ አልፎ ለመሄድ ብቻ በድንበሩ ክልል ያገኛቸውን አቶ አንዳርጋቸውን ይዞ፤ አድኖ ለመብላት ድንበሩን ጥሶ ሰርጎ ለገባው ወያኔ አሳልፎ መስጠቱ፤ በሰባዊ ታሪክ ሲወገዝ የሚኖርበት፤ ትውልድ የማይረሳው፤ ዘመን የማይሽረው፤ ከአራዊታዊ ተግባር የከፋ ግፍ ፈጽሟል። የእንግሊዝ መንግስትም የራሱ ዜጋ አቶ አንዳርጋቸው ታድነው ሲበሉ

ያሳየው አዝጋሚነት፤ አቶ አንዳርጋቸው ተበልተው እስኪአልቁ ድረስ በመብላት ላይ ላሉት አውሬ ፋታ ለመስጠት ያዘነበሉ አስመስሏቸውል።

ወያኔ በህዝባችን ላይ የሚያደርገውን ይህን አራዊታዊ ተግባር እያየን፤ የየመንን አስቆሮታዊ ባህርይ እየተራዳን፤ የእንግሊዝን መንግስት አዝጋሚነት እየተገነዘብን ዝም ማለት ቤተ ሰብነትን መርሳት፤ ለወገን አለማሰብና ሃይማኖትን መካድ ሆኖ ተሰምቶናል። ስለሰው ክብርና ልዕልና የሚገልጹትን ቅዱሳት መጻህፍት ያስተማሩን የመምህሮቻችን አጽም ይፋረዳናል። በቤተ መቅደስ የምናቀርበው ቅዳሴ ኪዳንና በአውደ ምህረቱ ላይ የምናነባቸው ቅዱሳት መጻሕፍት ከአውደ ምህረቱ ውጭ ወጥተን ከሚጮኸው ህዝብ ጋራ እንድንቀላቀል ያስገድዱናል።

የዘመናችን ቀሳውስት ጳጳሳትና ሰባኪዎች ቅዳሴውንና ስብከቱን “ያለዋጋ የተቀበላችሁትን ያለዋጋ ስጡ” ብሎ ክርስቶስ ካዘዘውና አባቶቻችን ቀሳውስት ሲመሩበት ከነበረው ባህል አውጥተን፤ የገንዘብ ምንጭ አድርገናቸዋል። ብንቀድስ ብንሰብክ ከምግባችን ጋራ በመያያዙ አያስደነቅምም አያስመሰግንምም። የሚያስደንቀውና የሚያስመሰገን ክርስቶስ “ያለዋጋ የተቀበላችሁትን ያለዋጋ ስጡ”ያለውን ስንፈጽም ብቻ ነው።

ህዝባችን በያለበት የሚያደርገው ሰላማዊ ሰልፍ፤ ”ሰማይ ስሚ“ እያለ የሚያሰማው ጩኸት፤ የገንዘብ ክፍያ ካለማስገኘቱ ባሻገር፤ ይልቁንም ከወያኔ መንግስት የምናገኘውን ጥቅም ስለሚነካ፤ በመግባትና በመውጣት በምናካሄደው ጥቅም ላይም ጉዳት ስለሚያስከትል፤ ዝም ብለን በመቀደስ፤ በመዘመር ህዝቡን ንስሀ ግባ፤ እያልን የራሱን ህሊና ከራሱ ጋራ እያጋጨን ፤ የወያኔን አራዊታው ተግባር እንዳይመለከት እንዳይሰማ እናፍዝዘው እናደንዝዘው ብለን ከወያኔ ጋራ የተባበርን ያስመሰለናል ብለን እጅግ ፈርተናል። የተማረውም ወገን ከሚወዳትና ከሚያከብራት ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያኑ በመሸሽ ላይ ያለው በአፍዛዥና አደንዛዥ አዚማችን ላለመያዝ ይመስለናል።

በህዝቡ መካል እየኖርን ፤ የሚበላውን እየበላን፤ የሚኖረውን ዓለማዊ ኑሮ እየኖርን በህዝብ ጉዳት ሲደርስ ”እንቀድስልሀልን፤ ንስሀ ግባ እንልሀለንና ከዚህ ሌላ ከኛ የሚጠበቅ የለም“ ማለት፤ ስለ ሰውነት ካስተማሩት ከነ መጥምቁ ዮሐንስ የበለጥን የንስሀ ጥሪ ሰባኪዎች ነን ማለት ይመስላል። ከላመ ከጣመ ምግብ ራሱን አግልሎ በምናኔ ሲኖር የህዝቡን መከራ በሰማ ጊዜ ከመነነበት ዋሻ ወጥቶ ህዝቡን ከተቀላቀለው ከእንጦንስ እጅግ የላቁ፤ ዓለምን የናቁ መስሎ ለመኖር ማሰብም ይቅርታ የሌለው ማተለልና በደል ነው።

ተሰደናል እያልን ከተሰደደው ህዝብ ጋራ ተቀላቅለን የህዝባችንን ብሶት ለመግለጽ ባለመተባበራችን ህዝበ ክርስቲያኑ “የዘመናችንን ካህናት በተለይም በጳጳሳት ላይ እግዚአብሔር ይይላቸው” እያለ እንጅ፤ ቅዳሴውን ለዕለት ገቢያችን ስንል ብቻ እንደምናካሄደው ቀደም ብሎ ታዝቦናል። ወገኑ አካሉ እንዳልሆን እምነትም እንደሊለን ተረድቶናል። ከኛ ከካህናቱ ይልቅ ራሱ ህዝባችን ለሃይማኖቱና ለባህሉ የተሻለ አክብሮትና ፍቅር ስላለው እኛን እየታዘበ ለፈጣሪ የገባውን ብጽአት (እኛ የምንበላውን) ባለማቆ ሙ እንደ ሞኝ ልንቆጥረው አይገባም።

እኛ ከላይ ስማችንን የገለጽን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቀሳውስት፤ እስካሁን በህዝባችን ላይ የወደቀውን ብሶቱን መከራውን ሀዘኑን በሚያመረቃና በተቀናበረ መንገድ መመስከር አለመቻላችን በስደተኛው ህዝብ ላይ የፈጽመነው በደል ይሰማናል።

ካህናት የጦርነትን አዋጅ ደግፈን ባናውጅም፤ ህዝባችን እኛ፤ እኛም ህዝባችን ነንና በሰውነታችን የተተከለብንን እሾህ እየነቀልን እንድንጮህ፤ እየጮህንም የተከለብንን እሾህ ለመንቀል ሃይማኖታችን ሰውነታችን ዜግነታን ታሪካችን ያስገድደናል። ኢትዮጵያውያን በአራዊት ባህርይ ከፈረጁት ከኢሀደግ ጋራ ተባብሮ የየመን መንግስት በአቶ አንዳርጋቸው ላይ የፈጸመውን አራዊታዊ ባህርያ እናወግዛለን። የእንግሊዝ መንግስትም ባንድ ዜጋው ላይ ይህን የመሰለ ደባ ሲፈጽም፤ በጠላት እጅ ውሎ ሲያድር የሚደርስበትን የሰውነትና የሞራል ውድቀት በመገንዘብ ያለውን ኃይል ተጥቅሞ ለመታደግ የሚያደርገውን ፈጣን ርምጃ እንዲወስድ እንማጸናለን።

<u>ቤተ ክርስቲያናችን እግዚአብሔርንና ህዝባችንን በቅስና እንድናገለግል ስትሰይመን፤ ከፉ ዘመን የወለደው ሲኖዶስ ሃይማኖት ሲክድ ካዱ። ሲያምን እመኑ። ሲኖዶስ በህገ አራዊት ከሚመራ መንግስት ጋራ ተባብሮ እምነትን ሲያዛባ፤ በፍትህ ላይ ሲቀልድ፤ ዝሙት ሲፈጽም፤ በብዝበዛ ሲሰማራ ተባበሩ ብላ አይደለም። ያያችሁትን እውነት መስክሩ ! የሰማችሁትን ሃሰት ባደባባይ ተቃወሙ ! እግዚአብሔር በአርያው ለፈጠረው ሰው ሁሉ ክብር ዘብ ቁሙ“ ብላ ነው።</u>

በስደት ዓለም ካሉት በሽህ ከሚቆጠሩት ቀሳውስት በላይ እውቀት ችሎታና ብቃት አልን ብለን አይደለም። በወያኔ ተገደንም ሆነ ወደን፤ መጠቀሚያ ከመሆን ለሰወረን አምላክ የምናቀርብለት መስዋዕት ሆኖ ስለታየንና በአገር ውስጥ እንዳይናገሩ ታፍነው ከተያዙት ወገኖቻችን ትዝብት ለመዳን ከውዴታ ግዴታ ሃላፊነት ይልቅ እጅግ በጣም የከበደውን የግዴታ ግዴታችንን ለመወጣት ስንል ይህችን መግለጫ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ስም ለመላ ኢትዮጵያውያን አቅርበናል።

ካሁን ጀምሮ በህዝባችን ላይ እየደረሰ ያለውን ግፍና መከራ ካባቶቻችን ሊቃውንት በተማርነው መንገድ እየተከታተልን ቅድስት ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያናችን በምትፈቅድልንና በሰጠችን ክህነታዊ ስልጣንና ሀለፊነት ለህዝባችን ማቅረቡን እንቀጥላለን። ፈቃደኞች የሆናችሁ ቀሳውስት ተባበሩን።

እግዚአብሔር የመከራችንን ዘመን እንዲያሳጥርልን ተግባር ያልተለየው ጸሎት እናቅርብለት።